# ጉም ጉም!

ጉም ጉም እንዲያው ጉምዳ፤
አበሽ መጣብህ እዳ፤
ሳትዘጋጅ ሳትሰናዳ፤
ደርሶ ወራጅ እንደንግዳ፤
ሊፈነዳ ሊፈነዳዳ፤
እንዲያው ጉም ጉም ጉምዳ፤
ዱብ ዱብ ዱብ ወይ እዳ!

ሶስተኛ ዙር በደረቁ፤
ሳይዘጋጁ ሳይታጠቁ፤
ሳይገምቱ ሲንቁ ሲያናንቁ፤
ሲደብቁ ሲደባበቁ፤
ሲዘብቱ ሲዘባበቱ፤
ሲደክሙ ሲረኳኮቱ፤
ደረሰች ጊዜ ተጉዛ፤
የአሁኑስ ከቶም አያዋዛ።

ሲነገረው አልሰማ ብሎ፤
መሰብሰብ መዘጋጀቱን ጥሎ፤
ሊያሳልፈው ለመጋኛ፤
እንደገና ዳግመኛ ሶስተኛ።

ጉምጉም እንዲያው ጉምጉም፤
ነገሩ ነገሩን አናውቅም፤
ይሸታል ይነፍሳል ነፋስ፤
ሽው ሽው ይላል ሲደርስ።

አጣረም ሞተ ተኛ፤
የኛ ሰው አይደገኛ፤
አይናገር በዋዛ፤
ምንም ምስጢር ቢበዛ፤
መውጣቱ አይቀርም፤
አልተደበቀም ምንሊክም፤
ቢበዛ ሁለት አመት፤
ሸሽገው ቢያቆዩት።

ችግሩ መች ሆነና፤
የግለሰብ የዝና፤
የአገር የሕዝብ ገመና፤
እንጂ የህልውና፤
ብሎም የልእልና።
ሁሉን ጠቅልሎ ለብቻው፤
ቀፍድዶ ጠፍሮ ከጓዳው፤
እንዳይሆን ማደረጉ ጣጣ፤
ጉድ ፈላ እዳ መጣ።

የሰፈነው ምስቅልቅል፤

የተተበተበው ዝብትልትል፤

ለመፍታት አስቸጋሪ፤

አገሬ ይህን ፍሪ፤

ካለውል ስታደሪ፤

ልእልናሽን ጠንግሪ፤

በጊዜ ቶሎ አብሪ።

ከእንግዲህ የለም እንደነበር፤

መቀጠል አይቻል ነገር፤

ወይ ነጣነት ወይ ባርነት፤

አንዱን ምረጥ ከሁለት!!!!!!!!

ፍ አ

07 10 2012